## የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ - ኢሰመጉ

**ኢሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!**

# <u>በማይካድራ ከተማና አካባቢው ላይ በተፈጸመው ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የኢሰመጉ የመስክ ምርመራ ግኝት የመጀመሪያ ደረጃ (ቀዳሚ) ዘገባ</u>

**ታህሣሥ 16 ቀን 2013 ዓ.ም**

**የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ - ኢሰመጉ** ከጥቅምት 25 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ በትግራይ ክልል እና አዋሳኝ አካባቢዎች፤ በትግራይ ክልል መንግሥት እና በፌዴራል መንግሥት መካከል የነበረውን የትጥቅ ግጭት በከፍተኛ ትኩረት ሲከታተለው ነበር። ኢሰመጉ ግጭቱ ከተከሰተበት ቀን አንስቶ ባሉት ተከታታይ ቀናት ባወጣቸው ማሳሰቢያዎች ግጭቱ በምንም ዓይነት ሁኔታ ያልታጠቁ ሰላማዊ ሰዎችን ደህንነትና የሲቪል ንብረቶችን አደጋ ውስጥ የሚከት እንዳይሆን ሲወተውት ቆይቷል። ሆኖም፤ በግጭቱ ወቅት በሰላማዊ ሰዎች ላይ የተፈጸሙ አሰቃቂ ግድያዎችና ጾታዊ ጥቃቶችን ጨምሮ ለልዩ ልዩ አካላዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጉዳቶች እንዲሁም ከፍተኛ ለሆነ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሰለባ ሆነዋል። ከእነዚህ መካከል ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም በማይካድራ ከተማ የተፈጸመው የብዙኃን ግድያ እና ወንጀል ዋነኛው ነው።

ኢሰመጉ፤ ሁኔታውን ለማጣራት የሰብዓዊ መብቶች ባለሙያ ቡድን አዋቅሮ ወደ ሥፍራው በመላክ በወቅቱ የተፈጸመውን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ምንነት የመለየት ሥራ ከህዳር 24 - ታህሳስ 2 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ በማይካድራ፣ ሁመራ፣ አብደራፊ፣ አብርሀጅራ፣ ዳንሻ እና ጎንደር ከተሞች ተዘዋውሮ የመስክ ምርመራ ሥራ አከናውኗል። የምርመራ ቡድኑ በተጠቀሱት አካባቢዎች ተዘዋውሮ የሟች ቤተሰቦችን፣ በጥቃቱ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን፣ የዓይን ምስክሮችን፣ የቀብር ስርዓቶችን ያከናወኑ ሰዎችንና የቤተ-ክርስትያን አባቶችን፣ በጊዜያዊነት የተቋቋሙ የመንግሥት ተቋማት የሥራ ኃላፊዎችንና ሌሎችም የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሞ ልዩ ልዩ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን አሰባስቧል። ከእዚህ በተጨማሪ፤ ቡድኑ በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ እና ከቤተ-ክርስቲያን ቅጥር ውጪ የሚገኙ የጅምላ መቃብሮችን ተዘዋውሮ የጎበኘ ሲሆን፤ በምርመራ ሥራው ወቅት አሁን ድረስ ያልተነሱ እና የቀብር ስርዓት ያልተፈጸመላቸው አስከሬኖችን ጭመር አግኝቷል።

### <u>የምርመራ ሥራው ዋና ዋና ግኝቶች</u>

በማይካድራ ከተማና ዙሪያዋ ያለውን ሰፋፊ የሰሊጥና ማሽላ እርሻዎች ተከትሎ የወቅት ሥራ የሚሠሩ በልማድ ‹‹ሳሉግ›› በመባል የሚጠሩ የጉልበት ሠራተኞች በብዛት የሚኖሩ ሲሆን፤ በተለምዶ ‹‹የጡት

እናት/አባት›› በመባል በሚጠሩ ቤቶች ውስጥ በርከት ብለው የሚያድሩ ናቸው። በጥቃቱ ሰለባ የሆኑት በአብዛኛው እነዚሁ በቀን ሥራ ላይ ተሠማርተው የሚኖሩ ሰላማዊ ሰዎች ናቸው።

የትጥቅ ግጭቱ ከተነሳበት ቀን ጀምሮ በትግራይ ክልል መንግሥት እና በፌዴራል መንግሥት የፀጥታ ኃይሎች መካከል በከተማዋ አዋሳኝ አካባቢዎች ላይ ይደረግ በነበረው ከፍተኛ ግጭት የተነሳ የከተማዋ ነዋሪዎች፣ በተለይም የሌላ ብሔር ተወላጆች ከባድ ስጋት ውስጥ ገብተው ነበር። የማይካድራው ድርጊት ከመከሰቱ ሁለት ቀናት አስቀድሞ የማይካድራ አካባቢ ፖሊስ እና የትግራይ ልዩ ኃይል መረጃ ታቀብላላችሁ በሚል የሱዳን ሲም ካርድ የያዙ ሰዎችን ቤት ለቤት በተደረገ ፍተሻ ያጣራ ሲሆን፤ በፍተሻው የተገኙ ሲም ካርዶች ተሰብስበረዋል። በሁኔታው ስጋት የገባቸው ሰዎች በተለይም ወደ አማራ ክልል ለመግባት ያደረጉት ሙከራ፤ ሁሉም መውጫ መንገዶች በትግራይ ልዩ ኃይልና ሚሊሻ አባላት የተዘጉ በመሆኑ መውጣት ሳይችሉ ቀርተዋል።

በእለቱ (ጥቃቱ በተፈጸመበት ቀን ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም) የፖሊስና የልዩ ኃይል አባላት እንዲሁም የትግራይ ተወላጅ ወጣቶች (በአብዛኛው በልዩ ስሙ ‹ሣምሪ› ከሚባል ሰፈር የመጡ) ማንም ሰው ከቤት እንዳይወጣ ትዕዛዝ መስጠታቸውን የጥቃቱ ተጎጂዎች ተናግረዋል። ወጣቶች በብዛት ሆነው በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ሲጨፍሩ እንደነበር እና በአንድአንድ ቦታዎች ከቀኑ 5:00 ጀምሮ በአብዛኛው የአማራ ብሔር ተወላጆች የሚኖሩበት ልዩ ስሙ ‹‹ግምብ ሰፈር›› በሚባለው አካባቢ ደግሞ ከ 9:00 ጀምሮ የትግራይ ተወላጅ የሆኑና ያልሆኑ ሰዎችን ለመለየት መታወቂያ በማየት እና በትግረኛ ሲያናግሯቸው መልስ መስጠት የማይችሉ ሰዎችን ለይተው ጥቃቱን ማድረስ እንደጀመሩ ተጎጂዎች ቃላቸውን ሰጥተዋል።

ጥቃቱ በአብዛኛው ገጀራ፣ ጩቤ፣ ፊራድ (መጥረቢያ) እና ገመድ የመሳሰሉ መሳሪያዎችን በመጠቀም የተፈጸመ ሲሆን፤ ዒላማ ያደረገው ደግሞ በአብዛኛው ወጣት ወንዶችን መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ጥቃቱ በግልጽ የብሔር ማንነትን መሠረት ያደረገ እና በአብዛኛው የአማራ ብሔር ተወላጅ በሆኑ ሰዎች ላይ ያነጣጠረ ሲሆን፤ በቁጥር አነስተኛ የሚባሉ የሌሎች ብሔር ተወላጆችም የጥቃቱ ሰለባ እንደሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል። ድርጊቱ በዋናነት ማይካድራ ከተማ ውስጥ ‹ሣምሪ› ከተባለ ሰፈርና ከሌሎችም ቀበሌዎች በመጡ በቡድን የተደራጁ የትግራይ ተወላጅ ወጣቶች ሲሆን፤ እያንዳንዱ የወጣቶች ቡድን በትግራይ ልዩ ኃይልና ሚሊሻ አባላት በጦር መሳሪያ የታገዘ ሽፋንና ድጋፍ ይደረግላቸው እንደነበር ተጎጂዎች ከሰጡት ቃል ለመረዳት ተችሏል።

በጥቃቱ ሕይወታቸውን ያጡ ሰዎችን ፍለጋና ቀብር ከህዳር 2 – 6 ድረስ ባሉት ተከታታይ ቀናት የተከናወነ ሲሆን፤ ከእነዚህ መካከል በማይካድራ ከተማ አቡነአረጋዊ ቤተ-ክርስቲያን ብዛታቸው 86 የሚሆኑ እያንዳንዳቸው በአማካይ ከ 5 - 10 ያህል ሰዎች የተቀበሩባቸው የመቃብር ስፍራዎችን እና በወቅቱ አስከሬኖች ተጭነው የመጡባቸው በርካታ አልጋዎችን ለማግኘት ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪ፤ ከቤተ-ክርስቲያኑ ቅጥር ውጪ በቅርብ ርቀት ላይ 42 ሰዎች፣ ስለላ መስመር በሚባለው አካባቢ 57 ሰዎች፣ ወልደ አብ መንገድ ላይ 56 ሰዎች፣ ቀበሌ 04 ድልድይ አካበቢ 6 ሰዎች፣ በአቅራቢው ካለ ጎርፍ መውረጃ አካባቢ 18 ሰዎች የተቀበሩባቸው የጅምላ መቃብሮች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል።

ተጎጂዎች በፍለጋው ወቅት አስከሬናቸው አሁን ድረስ ያልተገኙና ያልተቀበሩ መኖራቸውንም ያሳወቁ ሲሆን፤ ይህንንም የኢሰመኮ የምርመራ ቡድን አባላትም ያልተነሳ አስከሬን በዓይናቸው ዓይተው አረጋግጠዋል።

በተጨማሪም፤ በአንዳንድ ቦታዎች አካባቢው በጣም ሞቃታማ በመሆኑ ምክንያት የሚኞች አስከሬን ለማንሳት እጅግ አስቸጋሪ በመሆኑ ባለበት ቦታ እንዲቀበሩ መደረጉን አስረድተዋል።

የምርመራ ቡድኑ ከማይካድራ ከተማ በተጨማሪ ተመሳሳይ ጥቃቶች በሁመራ እና ዳንሻ ከተሞች ላይም መፈጸሙን አረጋግጧል። በሁመራ ከተማ 6 ሰዎች በገጀራ፣ በመጥረቢያ እና በጥይት ተመትተው መገደላቸውን፣ አስከሬናቸው ሳይነሳ ፀሀይ ላይ በመቆየቱ ማንሳት ስላልተቻለ ልዩ ስሙ ‹አንድሪስ› በሚባል አካባቢ መቀበራቸውን ከሟች ቤተሰቦች ለማረጋገጥ ችሏል። በዳንሻ ከተማ ደግሞ እድሚያቸው የ 12 እና የ 15 ዓመት የሆኑ ህጻናት በመጥረቢያ ተመትተው መገደላቸውን እና ቀብራቸውም በጊዎርጊስ ቤተ-ክርስቲያን የተፈጸመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

በዚህ መልኩ በተፈጸመው ጥቃት ኢሰመጉ ባደረገው የመስክ ምልከታና ባሰባሰበው መረጃ ከ1100 በላይ የሚሆኑ ሰላማዊ ሰዎች ሕይወት ማለፉን አረጋግጧል። በጥቃቱ ከ122 ያህል በላይ ሰዎች የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን፤ በአብደራፊ እና ጎንደር ሆስፒታሎች ህክምናቸውን እየተከታተሉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም፤ ድርጊቱን ሲፈጽሙ የነበሩት ወጣቶች ንብረት ያወድሙና ይዘርፉ እንደነበር ተጎጂዎች ከሰጡት ቃል ለመረዳት ተችሏል።

በሌላ በኩል፤ የምርመራ ቡድኑ ጥቃቱ በተፈጸመበት እለት በማይካድራ ከተማ አስገድዶ መድፈርን የመሳሰሉ ጾታዊ ጥቃቶች መፈጸማቸውን የሚያሳዩ መረጃዎች አሰባስቧል። ስለ ሁኔታው ቃላቸውን የሰጡ ስድስት የጥቃቱ ሰለባዎች እያንዳንዳቸው ከ10 በላይ በሚሆኑ ጥቃቱን ሲፈጽሙ በነበሩት ወጣቶች የአስገድዶ መድፈር ወንጀል እንደተፈጸመባቸው ተናግረዋል። የምርመራ ቡድኑ አባላት በወቅቱ ቃላቸውን የሰጡ ተጎጂዎች በገልጽ በሚታይ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጉዳት ውስጥ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ችለዋል። ተጎጂዎቹ ከደረሰባቸው ጥቃት በኋላ ማንኛውም ዓይነት አካላዊም ሆነ ስነ-ልቦናዊ ህክምና ያላገኙ በመሆኑ፤ አፋጣኝ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ህክምና የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት እና የሰብዓዊ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ትኩረት እንዲሰጡት ኢሰመጉ ያሳስባል።

ከዚህ በተጨማሪ፤ በወቅቱ በማይካድራ ከተማ እና አካባቢዋ የነበረውን ሁኔታ ተከትሎ ለጊዜው ግምቱ በግልጽ ያልታወቀ ንብረት መውደሙን እና መዘረፉን፣ በርካታ ሰዎች ቤት ንብረታቸውን በመተው ወደ ተለያዩ አካባቢዎች መፈናቀላቸውን እና ድንበር ተሻግረው ወደ ሱዳን መሰደዳቸውንም የኢሰመጉ መርማሪ አባላት ለማረጋገጥ ችለዋል። በወቅቱ የጠፋውን የንብረት ውድመት፣ ዝርፊያ እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃይ እና ስደተኞች አጠቃላይ ዝርዝር ሁኔታ ኢሰመጉ በቅርብ ጊዜ ይፋ በሚያደርገው ጥቅል የሰብዓዊ መብቶች ዘገባ የሚዳስሰው ይሆናል።

በዚህ ብዙዎችን ሰለባ ባደረገው ድርጊት ሰዎች ጥቃት እንዳይደርስባቸው የተከላከሉ፣ የሸሸጉ እና መረጃ በመስጠት እንዲሸሹ በማድረግ ሰብዓዊ ተግባር የፈጸሙ የትግራይ ተወላጆች መኖራቸውንም የኢሰመጉ የምርመራ ቡድን ለማወቅ ችሏል። ምንም እንኳን የምርመራ ቡድኑ በዚህ ሰብዓዊና በጎ ምግባር የተሳተፉ የትግራይ ተወላጅ ሰዎችን በስጋት ምክንያት አካባቢውን ለቀው የወጡ በመሆኑ አግኝቶ ለማነጋገር ባይችልም፤ በዚህ ሰብዓዊ ምግባር ከጥቃቱ የተረፉ በርካታ ሰዎች ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

በመሆኑም፤ ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም በማይካድራ ከተማና አካባቢው ተፈጸመው ግፍ እና ጭካኔ የተሞላበት ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ያስከተለ ድርጊት መሆኑን ኢሰመጉ

ለማረጋገጥ ችሏል። ስለሆነም፤ ይኸን አሳዛኝ ድርጊት ያቀዱ፣ የፈጸሙ እና ያስፈጸሙ አጥፊዎች በሙሉ በተገቢው መንገድ ተጣርቶ በሕግ ፊት ሊቀርቡ እንደሚገባ ኢሰመጉ ያሳስባል።

ኢሰመጉ፤ የዚህ እጅግ አሳዛኝ ድርጊት ዝርዝር የጉዳት ዓይነትና መጠን፣ መነሻ ታሪክ፣ የሕግና ፍሬ ነገር ትንተና እና ምክረ-ሐሳብ የያዘ፣ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች የተሳተፉበት ጥቅል የሰብዓዊ መብቶች ዘገባ በቅርብ ጊዜ አጠናቅሮ ለሕዝብ ይፋ የሚያደርግ መሆኑን ያሳውቃል።

ታህሣሥ 16፣ 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ኢሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፣ የዓለም አቀፍ ጸረ-ሥቃይ ድርጅት (OMCT) አባል፣ የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ጥበቃ ኅብረት (Defend Defenders) መሥራች አባል ነው።